# ክልሎቹ ከወሰን ማካለል ጋር ተያይዞ የተፈጠረውን አለመግባባት ለመፍታት ተስማሙ

122 times

አዲስ አበባ ሚያዚያ 11/2009 በኦሮሚያና በሶማሌ ክልሎች መካከል ከወሰን ማካለል ጋር ተያይዞ የተፈጠረውን አለመግባባት መፍታት የሚያስችል ሥምምነት ተደረሰ።

ሥምምነቱን የኦሮሚያ ክልል ፕሬዚዳንት አቶ ለማ መገርሳና የሶማሌ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ አብዲ መሃመድን ጨምሮ የክልሎቹ ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች ፈርመውታል።



ቀደም ሲል በሁለቱ ክልሎች አጎራባች ወረዳዎችና ቀበሌዎች በሚኖሩ ሕዝቦች መካከል ሊከሰቱ የነበሩ አለመግባባቶችን ለማስቀረት ማኅበረሰቦቹ በመረጡት ክልል እንዲተዳደሩ ተደርጓል።

የፌዴሬሽን ምክር ቤት በወሰነው ውሳኔ መሰረትም ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ጥቅምት 14 ቀን 1997 ዓ.ም በሁለቱ ክልሎች አዋሳኝ በሆኑ 422 ቀበሌዎች ሕዝበ ውሳኔ ማካሄዱ ይታወሳል።

በቦርዱ ውሳኔ መሰረትም በሁለቱ ክልሎች የሚኖረውን አስተዳደራዊ ወሰን መለየት እንዲቻል የፌዴራል ጉዳዮችና አርብቶ አደር አካባቢ ልማት ሚኒስቴር የወሰን ማካለል ሥራ ሲሰራ ቆይቷል።

በተለይም ከ2004 እስከ 2006 ዓ.ም የተካሄደው የወሰን ማካለል ሥራ የአካባቢው አስተዳደርና ኅብረተሰቡ በንቃት የተሳተፉበት በመሆኑ አመርቂ ውጤት ማምጣት ተችሏል።

ይህን ልምድ በመውሰድ ውስብስብ ችግር በታየባቸው በምስራቅና ምዕራብ ሐረርጌ፣ በፋፈን፣ በበነንቦና ሲቲ ዞኖች ሥር በሚገኙ የተወሰኑ አካባቢዎች የማካለል ሥራዎች ተሰርተዋል።

በተለይም ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ ተደጋጋሚ ውይይቶችና ምክክሮች እንዲሁም ኮሚቴ በማዋቀር መፍትሄ ለማምጣት ጥረት ቢደረግም ውጤታማ ባለመሆኑ ለዜጎች ህይወት ማለፍ ምክንያት ሆኗል ተብሏል።

የዛሬውም ሥምምነት ቀደም ሲል በተጠናቀቁት ላይ ተጨማሪ ሥራዎችን ለማከልና አለመግባባቶችን በዘላቂነት ለማስቀረት ያለመ መሆኑ ተነግሯል።

በሁለቱ ክልሎች መንግሥታት የፌዴራል አካላትና በሕዝቡ የጋራ ጥረት ሥምምነት ላይ ደርሰው ወደ ተግባር የገቡትን አካባቢዎች የወሰን ማካለል ሥራም ይጨምራል ተብሏል።

ስምምነቱ በሰባት ዞኖች 33 ወረዳዎች ሥር በሚገኙ 147 ቀበሌዎችና መንደሮች መካከል አስተዳደራዊ ወሰን ማካለልንም ያጠቃልላል።

በመሰረታዊነት አጎራባች ማኅበረሰቦችን በልማትና በመልካም አስተዳደር በማስተሳሰር ተጠቃሚ ለማድረግ እንደሚረዳ ተሰምሮበታል።

በእነዚህ አካባቢዎች እንዲሁም በአገሪቷ አስተማማኝና ዘላቂ ሠላም ማረጋገጥ የሚያስችል ሥምምነት መሆኑም እንዲሁ ተጠቅሷል።

የሁለቱ ክልሎች ርዕሰ መስተዳድሮችም የተደረሱ ሥምምነቶችን ለመተግበርና በአካባቢው ልማትና መልካም አስተዳደር ለማስፈን እንደሚሰሩ አረጋግጠዋል።

ጎን ለጎንም በሁለቱ ክልሎች ሕዝቦች መካከል ግጭት እንዲቀሰቀስ ያደረጉ ወንጀለኞችን ለሕግ ለማቅረብ እንደሚሰራ የፌዴራል ጉዳዮችና አርብቶ አደር አካባቢ ልማት ሚኒስቴር አስታውቋል።